DISTRICT OF COLUMBIA
OFFICE OF THE STATE SUPERINTENDENT OF
EDUCATION

ውድ ወላጅ ወይም አሳዳጊ፣

በጸደይ 2019፣ የእርሶ ልጅ የበርካታ-ክልል አማራጭ ምዘና (MSAA) በእንግሊዝኛ ቋንቋ አርት (ELA)/የማንበብ እና የመጻፍ ችሎታ እና ሂሳብ ምዘና ወስዶ ነበር። MSAA ከፍ ያለ የማገናዘብ ጉድለቶች ላሏቸው ተማሪዎች ሰፋ ላለ የድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ውጤት ለማዘጋጀት፣ ከፍተኛ የአካዳሚክ ውጤቶች ጭማሪ ለማበረታታት የታቀደ የተቀናጀ የምዘና ሲስተም ነው።

አባሪ የተደረገው መምሪያ ከልጅዎ የውጤት ሪፖርት ሊማሯቸው የሚችሉትን አስፈላጊ ነጥቦች ይመራዎታል። በተጨማሪ ልጅዎ በመጪው አመት እንዲያሻሽል እንዲረዳው ግብአቶችን ያቀርብሎታል።

ከ3-8 እና 11ኛ ላሉ ክፍሎች ለአማራጭ ምዘናው ብቁ የሆኑት የMSAA በELA/የማንበብ እና የመጻፍ ችሎታ እና ሂሳብ አስፈላጊ ነው። MSAA  ተማሪዎች በነጻነት ምላሽ እንዲሰጡ የሚረዳ አብሮ የተገጠመለት በዋናኝነት ኦንላይን የሚተዳደር ነው።  በተማሪዎቹ የግል ፍላጎቶች መሰረት በማድረግ፣ የተወሰኑ ተማሪዎች ከኮምፒውተሩ ጋር በቀጥታ ግንኙነት  የሚኖራቸው ሲሆን ሌሎች ደግሞ በፈተና አስተዳዳሪ በተዘጋጀ የጽሁፍ ሰነዶች አማካኝነት ግንኙነት ይኖራቸዋል።

በመጨረሻ፣ የኛ እቅድ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ ስኬታማ ለመሆን እና ህልሞቻቸውን እና ፍላጎቶቻቸውን ለማሳካት መዘጋጀታቸውን ማረጋገጥ ነው። እርስዎ ስለምዘናዎች አጠቃላይ ጥያቄዎች ካሎት ወይም የበለጠ መረጃ ከፈለጉ፣ እባክዎ የኛን ድህረገጽ ይጎብኙ በ https://osse.dc.gov/service/alternate-assessments ወይም ከልጅዎ አስተማሪ ጋር ይወያዩ።

OSSE ውስጥ፣ በሁሉም ተማሪዎች እምቅ ችሎታ እናምናለን፣ እና ሁሉም ተማሪዎች መማር እንደሚችሉ እና ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሊደርሱ እንደሚችሉ እናምናለን። ልጅዎ እንዲሳካለት ከእርስዎ ጋር አጋር ሆነን መስራቱን እናደንቃለን።

እናመሰግናለን፣

Hanseul Kang
የDC የመንግስት የትምህርት ተቆጣጣሪ

# የውጤት ሪፖርቱን መከፋፈል፣ የፊት

ይህ መምሪያ ከልጅዎ የውጤት ሪፖርት ሊማሯቸው የሚችሉትን አስፈላጊ ነጥቦች ይመራዎታል። በተጨማሪ ልጅዎ በመጭው አመት የእርሱን ወይም የእርሷን አፈጻጸም እንዲያሻሽል የሚረዳ ጠቃሚ ግብአቶችን ይሰጥዎታል።

---



## ሂሳብ

**ጆሴፍ ቴስታከር**
የትም PCS

**የ 3ተኛ ክፍል የምዘና ውጤቶች**

**ስለዚህ ምዘና በተመለከተ**

ጆሴፍ የከአንድ በላይ ክልል አመራጭ ምዘናን በ (Multi-State Alternate ...ment, MSAA) በጸደይ 2019 ሂሳብ ተፈትኗል። MSAA ዲዛይን ... ከፍተና የአእምሮ አካል ጉዳት ላለባቸው ልጆች ነው። ለ DC ይዘት ... የታለመን እና የሚደረስን የትምህረት ይዘት ይመዝናል። የ MSAA ግብ ...አእምሮ ግብ ያላቸውን ተማሪዎች ከፍተኛ የሆነ የሚጨርም የትምህርት ... ለማስመዝገብ ይችሉ ዘንድ እና ለከፍተኛ ትምህርት ዝግጁ ሆነው በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መውጣት ይችሉ ዘንድ ማስቻል ነው።

የ MSAA ውጤቶች የጆሴፍን አፈጻጸም በትምህርት ይዘት እና ክህሎት ላይ ለመመዘን ከሚያስችሉ ብዙ መንገዶች አንዱ ነው። እኒዘህ ውጤቶች ከ ጆሴፍ የግል ትምህርት ፕሮግራም (Individualized Education Program, IEP) እድገት ሪፖርቶች፣ የተማሪ ስራ፣ የህክምና ምርመራዎች እና የአስተማሪ ግብረመልስ ጋር አንድ ላይ ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው። አንድ ላይ፣ እነዚህ ሙሉ የሆነ ምስል በ ጆሴፍ እድገት ላይ ያሳያሉ።

ስለዚህ ሪፖርት ጥያቄ ያለዎ ከሆነ፣ እባክዎ ከ ጆሴፍ አስተማሪ ወይም ዳይሬክተር ጋር ያውሩ ወይም **የትም ቦታ** PCSን በ (202) 719-0271 ያግኙ። ስለ MSAA ፈተና ጥያቄ ያለዎ ከሆነ፣ እባክዎ OSSEን በ (202) 719-6500 እና osse.dc.gov/service/alternate-assessments ያግኙ።

**ይሄንን ሪፖርት እንዴት ለመጠቀም ይችላሉ?**

ይህ ሪፖርት ስለ ጆሴፍ ክህሎት ጥያቄዎች ለመመለስ ይችሉ ዘንድ ይረዳዎታል፣

- በዚህ ምዘና ላይ የጆሴፍ ውጤት ምን ይመስላል?
- በዚህ ትምህርት ላይ የጆሴፍ ጥንካሬዎች እና ደከመቶች ምንድን ናቸው?
- የጆሴፍ ውጤት ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ሲነጻጸር ምን ይመስላል?

**በሂሳብ ምዘናው ላይ የጆሴፍ አፈጻጸም ምን ይመስላል?**

ይሄ ክፍል በምዘናው ላይ ልጅዎ ያገኘውን ጠቅላላ ውጤት ያሳዮታል። ይህ ጠቅላላ ውጤት ተማሪው በምን ደረጃ ላይ ነው ያለው የሚለውን ለማወቅ ይረዳል።

የአፈፃፀም ደረጃ
ደረጃ 3
ውጤት
1242

ደረጃ 3 ውጤት ያመጡ ተማሪዎች
መካከለኛ ውስብስብነት ያላቸውነው
ተግባራት ማጠናቀቅ ይችላሉ።



- **ደረጃ 1** የሚጠበቅበትን እስካሁን አላሟላም
- **ደረጃ 2** በከፊል የሚጠበቅበትን አሟልቷል
- **ደረጃ 3** የሚጠበቅበትን አሟልቷል*
- **ደረጃ 4** ከሚጠበቅበት በላይ አሟልቷል*

* ደረጃዎች 3 እና 4 ከሁለተኛ ደረጃ ለመውጣት እና ወደ ከፍተኛ ትምህርት ለመግባት ዝግጁ ነው የሚለውን ያሳያሉ

**የበለጠ ለማወቅ ይፈልጋሉ?**

በምዘናው ቁልፍ ቦታዎች ላይ ጆሴፍ ያለው አፈጻጸም ምን ይመስላል የሚለውን ለማየት እና የጆሴፍ ውጤት ከሌሎች ተማሪዎች አንጻር ምን ይመስላል የሚለውን ለማየት ወደሚቀጥለው ገጸ ይሂዱ።

### 1) የምዘና መግለጫ

የምዘናው አጭር መግለጫ በሪፖርቱ በላይኛው ክፍል ይገኛል። ስለዚህ ሪፖርት ማንኛውም ጥያቄዎች ካሎት በዚህ አንቀጽ ታች ማግኘት ያለብዎትን ሰው መረጃ አለ።

### 2) ልጅዎ በአጠቃላይ አፈጻጸሙ እንዴት ነው?

የልጅዎ ውጤት ከአራቱ የአፈጻጸም ደረጃዎች አንዱ ላይ ያርፋል። የአፈጻጸም ደረጃው የልጅዎ ውጤት የት ላይ እንደሚያርፍ እና ልጅዎ ለክፍሉ ደረጃ የሚጠበቅበትን ማሟላቱን ይለያል። ደረጃ 3 ወይም 4 ውጤት ማለት ልጅዎ በዚያ የትምህርት አይነት የሚጠበቅበትን አሟልቷል ወይም ከሚጠበቅበት በላይ ሰርቷል ማለት ነው። ከደረጃ 2 በታች ውጤት ያላቸው ተማሪዎች ለክፍሉ ደረጃ የሚመጥን ክህሎቶችን እና እውቀት እያዳበሩ ሊሆን ይችላል።

# የውጤት ሪፖርቱን መከፋፈል፣ የጀርባ

### 3) ተማሪዎ ልዩ እውቀት እና ክህሎቶችን ምን ያክል ተማረ?

ተማሪዎች ሊያሳይዋቸው ስለሚችሉ ጥንካሬዎች እና ከአፈጻጸም ደረጃቸው በኋላ ሊያከናውኗቸው ስለሚችሉ አጠቃላይ ስራዎች የበለጠ ዝርዝር መረጃ ይደርሳቸዋል።



3 ተኛ ክፍል የሂሳብ ዝርዝሮች

የአፈፃፀም ደረጃ

ደረጃ 3

**ቁልፍ በሆኑት ምርመራዎች ላይ የጆሴፍ ውጤት ምን ይመስላል?**

ረጃ 3 ተማሪዎች

ህ ደጀራ ላይ ያሉ ተማሪዎች ውስብስብነቱ መካከለኛ የሆነን ተግባር ማጠናቀቅ ላሉ። ይህም የሚታወቁ ችግሮችን በሂሳባዊ አውድ እንዲሁም የተለያዩ ማለጫዎች እና ምልክቶች ጭምር የሚያካትት ነው።

ተማሪዎች በጠቅላላው የሚተለውን ማድረግ ይችላሉ፣

- መደመር እና መቀነስ ያላቸውን መልመጃዎች መስራት
- ከአንድ አውድ አንጻር የአንድን መልስ ትክክለኛነት ማረጋገጥ
- የማባዛት ቀመሮችን ሁለቱም ቁጥሮች ከአምስት እኩል ወይም በታች መስራት
- የብዜት ንድፎችን መለየት
- የክፍልፋይ ሞዴሎችን ከ ቁጥር ክፍልፋዮች ጋር ማዛመድ
- ክፍልፋዮችን ከተለያዩ ላእላዮች እና አንድ አይነት ታህታዮች ጋር ማነጻጸር
- አንድን ዳታ ከአንድ ዝርዝር ወደ ባር ግራፍ ማዞር

በዚህ ደረጃ ላይ ያሉ ተማሪዎች በጣም ውስብስ የሆኑ ተግባራት ይቀርቡላቸዋል። እነዚህም ብዙ የሂሳብ ሀሳቦችን በመልመጃዎች ውስጥ የሂሳብ ቀመሮችን፣ ቁጥሮችን ምልክት በመጠቀም መገለጽ እና ሌሎች ነገሮችን ጨምሮ የሚቀርቡ ሀሳቦችን የሚያካትት ነው።

ተማሪዎች በጠቅላላው የሚተለውን ማድረግ ይችላሉ፣

- ቁጥሮችን ቅርብ ለሆነው 10ኛ ማጠጋጋት
- እኩል ሁለት ቦታ የተከፈሉ የጂኦሜትሪ ምስሎችን መለየት።
- የአንድን አራት መአዘን ስፋት ለማስላት ስኩዌሮችን መቁጥር

**የጆሴፍ አፈጻጸም እንዴትን ይነጻጸራል?**

ጆሴፍ የትም PCS ውስጥ ካሉ የ 3ተኛ ክፍል ሂሳብ MSAA ፈተና ከወሰዱ ልጆች ውስጥ 99% ከሚሆኑት የተሻለ ውጤት አስመዝግቧል።

0 20 40 60 80 100

ጆሴፍ በ DC ውስጥ ካሉ እና የ 3ተኛ ክፍል ሂሳብ MSAA ፈተናን ከወሰዱ ልጆች ከ 78%ቱ የተሻለ ውጤት አስመዝግቧል።

0 20 40 60 80 100

**ከጥሎ የሚሆነው ምንድን ነው?**

ይሄንን ሪፖርት ከተማሪዎ መምህር ጋር በሚደረገው ቀጣዩ ስብሰባ ላይ ያምጡት። የጆሴፍን አስተማሪዎች መጠየቅ ይችላሉ:

- በዚህ አመት ጆሴፍ የሚማረው ሂሳብ ምንድን ነው?
- ጆሴፍ እንዴት ነው?
- ይህንን መረጃ በመጠቀም ከጆሴፍ ጋር በዚህ አመት መስራት የምችለው እንዴ ትኤ ነው?
- ጆሴፍን ለመደገፍ ምን አይነት ግብአበት መጠቀም አለብኝ?

የበለጠ መረጃ የት ማግኘት እንደሚችሉ መጠየቅ?

- የጆሴፍ ትምህርት ቤት እና ሌሎች ትምህርትቤቶች ውጤት የሚሰጣቸው እንዴት ነው፣ results.osse.dc.gov ይጎብኙ ወይም ለየትም PCS በ (202) 719-0271 ይደውሉ
- ፈተናው እንዴት እንደተዘጋጀ እና ምን እንደሚመዝን፣ osse.dc.gov/service/alternate-assessments ይጎብኙ ወይም ለ OSSE በ (202) 719-6500 ይደውሉ
- እነዚህን ሪፖርቶች ቤተሰቦች፣ አስተማሪዎች፣ እና ትምህርት ቤቶች ይጠቀማሉ፣ ይጎብኙ osse.dc.gov/parcc ወይም OSSE (202) 719-6500 ላይ ይደውሉ



### 4) እሱ ወይም እሷ ከሌላ ተማሪዎች ጋር ሲነጻጸር እንዴት ነው አፈጻጸማቸው?

ይህ ሪፖርት የተማሪዎ አፈጻጸም MSAAን በአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ ደረጃ፣ እና በግዛት ውስጥ ከወሰዱት የእርሱ ወይም የእርሷ አቻዎች ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ያሳያል።

### 5) ቀጥሎ ምንድን ነው?

በውጤት ሪፖርቱ ላይ ያለው መረጃ የተማሪውን እድገት ለመለካት እና የክህሎት ማዳበሪያ መምሪያን ለመስጠት የታለመ ነው። ይህ ክፍል የልጅዎን አስተማሪ ስለ ልጅዎ የእርሱ ወይም የእርሷ አፈጻጸም ሊጠይቋቸው የሚችሉ የተወሰኑ ጥያቄዎችን ያቀርባል። በተጨማሪ የበለጠ መረጃ የት ማግኘት እንደሚችሉ ያጋራል።